የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ጥር ፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22[nd] Year No. 22
ADDIS ABABA, 11[th] January, 2016


## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፸/፪ሺ፰ ዓ.ም


የምግብ፣ መድኃኒት፣ የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የአገልግሎት ክፍያ ተመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.................ገጽ ፰ሺ፯፻፳፱

ሠንጠረዥ.................................ገጽ ፰ሺ፯፻፴፭


## CONTENT

Regulation No.370/2015


Rate of Service Fees for Food, Medicine, Health Professional and Health Institutions Registration and Licensing Council of Ministers Regulation..............8729

Schedule.................................................8735


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸/፪ሺ፰

## የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት ክፍያ ተመንን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭፣ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፯ (፩) እንዲሁም በምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የምግብ፣ መድኃኒት፣ የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የአገልግሎት ክፍያ ተመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTER REGULATION No. 370/2015

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE FEE PAYABLE FOR REGISTRATION AND LICENSE OF FOOD, MEDICINE, HEALTH PROFESSIONAL AND HEALTH INSTITUTIONS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015, Article 17(1) of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 648/2009 and Article 55(1) of the Food, Medicine, and Health Care Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Rate of Service Fees for Food, Medicine, Health Professional and Health Institutions Registration and Licensing Council of Ministers Regulation No. 370/2015".

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩/ “አዋጅ” ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፪ሺ፪ ነው፣

፪/ “ደንብ” ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር ፪፻፺፱/፪ሺ፮ ነው፣

፫/ በአዋጁ እና በደንቡ የተጠቀሱ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፫. ስለ አገልግሎት ክፍያ**

፩/ የምግብ፣ የመድኃኒትና የኮስሞቲክስ አምራቾች አዲስ ፈቃድ ለማግኘት፣ በየጊዜው እድሳት ለማካሄድ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን፣ አዲስ የምርት መስመር ለማስፈቀድ፣ የአድራሻ ለውጥ የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ ሲኖርና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ እና ፪ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፪/ የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች፣ የኮስሞቲክስና የትምባሆ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይነት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት፣ በየጊዜው እድሳት ለማካሄድ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት፣ ሁለተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽንና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለመካሄድ፣ ተጨማሪ መጋዘን ለማስፈቀድ፣ የአድራሻ ለውጥ፣ የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ ሲኖርና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ፣ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፫ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

**2. Definition**

In this Regulation:

1/ “Proclamation” means the Food, Medicine, and Health Care Administration and Control Proclamation No. 661/2009;

2/ “Regulation” means the Food, Medicine, and Health Care Administration and Control Authority Regulation No.299/2014;

3/ definitions provided for under the Proclamation and the Regulation shall be applicable.

**3. Service fee**

1/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 1 and 2 attached to this Regulation for issuance of certificate of competence, renewal or replacement of certificates in case of loss for manufacturers in food, medicine and cosmetics, to issue permit for new processing line and to issue permit for changes in professionals and address of the institution, for second and third round of pre-license inspection, to permit a new method of manufacturing, for changes of the name of the institution and to issue permit for additional institution for the same purpose.

2/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 3 attached to this Regulation for issuance renewal and replacement of certificate of competence in case of loss for importers and wholesale of food, medicine cosmetics, medical equipment and supplies, and tobacco, to issue permit for additional storage and to issue permit for changes in professionals and address of the institution; for second and third round of pre-license inspection, for changes of the name of the institution and to issue permit for additional institution for the same purpose.

፫/ የጤና ተቋማት የመድኃኒት መግዣ ፈቃድ ለማግኘት፣ ለእድሳት እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፬ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፬/ ለጤና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬት ለማግኘትና ለእድሳት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፭ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፭/ ከውጭ አገር በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት ለሚመጡና ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ሄደው ለመሥራት ለሚፈልጉ የጤና ባለሞያዎች የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ሰርተፍኬትና በሥራ ላይ ያላቸውን አፈፃፀም መግለጫ ማስረጃ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፮ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፮/ የጤና ተቋማት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት፣ ለእድሳት፣ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን፣ አዲስ የአገልግሎት ዘርፍ ለመጨመር፣ የአድራሻ የባለሙያና የድርጅት ስም ለውጥ ለማድረግና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፯ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፯/ በመግቢያና መውጫ በር ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ወይንም ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ ምግብ ለቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፰ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፰/ በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ ለሚካሄድ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ፣ ኮስሞቲክስና

3/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 4 attached to this Regulation for issuance, renewal and replacement in case of loss of medicine purchase license for health institutions.

4/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 5 attached to this Regulation for issuance and renewal of health professionals' registration and license.

5/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 6 attached to this Regulation for issuance of registration certificate for foreign health professionals' to be employed in Ethiopia and to an Ethiopian health professional intending to work in a foreign country, and for issuance of letter of good standing.

6/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 7 attached to this Regulation for issuance, renewal and replacement certificate of competence in case of loss for health institutions, for second and third round of pre-license inspection, for changes of the name of the institution, professionals and the address of the institution itself and to issue permit for establishment of additional institution for the same purpose.

7/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 8 attached to this Regulation at the port of entry and exit for the inspection food which are to be imported and exported.

8/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 9 attached to this Regulation at the port of entry for import of medicines, medical raw materials, medical devices,

የኮስሞቲክስ ጥሬ ዕቃዎች፣ ትምባሆ ቁጥጥር፣ ለአስከሬን ቁጥጥር፣ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ ለሚበር አውሮፕላን ርጭት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፱ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፱/ በመውጫ በሮች ላይ ለሚካሄድ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ፣ ኮስሞቲክስና የኮስሞቲክስ ጥሬ ዕቃዎች እና የትምባሆ ቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲/ በውጭ ሀገር የሚገኝ የምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ እና ኮስሞቲክስ አምራች ወኪል ለመሆን ፈቃድ ለማግኘት፣ የወኪል ለውጥ፣ ተጨማሪ ወኪል ለማስመዝገብ ለእድሳት እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፩ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፩/ ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ለማስመዝገብ ለሰነድ ቅድመ ግምገማ ሥራ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ማጣሪያ ሰነድ ግምገማ ስራ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፪ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፪/ ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ለማስመዝገብ ወይም ለዳግም ምዝገባ ለሰነድ ግምገማ ሥራ፣ ለዋና እና አነስተኛ ልዩነት ምዝገባ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፫ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

cosmetics, cosmetics raw materials, tobacco, for undertake post mortem inspection and undertaking fumigation for airplanes departing from the country.

9/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 10 attached to this Regulation at the port of exit for inspection of export medicines, medical raw materials, medical devices, cosmetics, cosmetics raw materials and tobacco.

10/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 11 attached to this Regulation to give license of agent or change of agent, to register additional agent, for renewal and for replacement in case of loss of same for a foreign based food, medicine, medical devices and cosmetics manufacturers.

11/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 12 attached to this Regulation to register food, medicine, medical devices, medical equipment and supplies and cosmetics for pre-screening dossier evaluation, for second and third round documents pre-inspection.

12/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 13 attached to this Regulation for dossier evaluation to register or reregister food, medicine, medical devices and cosmetics and for registration of major or minor variation.

፲፫/ ለሚወገዱ ግብዓቶች ወይም ምርቶች በቦታው በመገኘት በአግባቡ መወገዱን ለማረጋገጥና ለሰርተፊኬት ዝግጅት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፬ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፬/ የመድኃኒት ምርት ሰርተፊኬት፣ ለሕክምና መገልገያዎች የተሰጠ የገበያ ፈቃድ ወይም ሰርተፊኬት እንዲሁም ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር የምግብ፣ መድኃኒትና ኮስሞቲክስ አምራቾች የመልካም አመራረት ስርዓትን ተከትለው ስለማምረታቸው የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማግኘት ወይም ሰርቲፊኬት ለማሳደስ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፭ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፭/ በውጭ ሀገር የሚገኙ የመድኃኒት አምራቾች በአገር ውስጥ ለሚከፍቱት ወኪል ቢሮዎች እውቅና ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፮ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፮/ ባለስልጣኑ ቁጥጥር በሚያካሂድባቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ወይም ፈቃድ ለማሳደስ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፯ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፯/ መድኃኒትን በአገር ውስጥ ለማስመዝገብና ለማስመጣት በውጭ ሀገር የሚካሄድ የመልካም አመራረት ቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፰ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፲፰/ የሕክምና ሙከራ ቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፲፱ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

13/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 14 attached to this Regulation to monitor a proper disposal of products or inputs ordered to be disposed and for preparation of certificate.

14/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 15 attached to this Regulation to issue or renew Certificate of Pharmaceuticals Products, Free Sale Certificate and Good Manufacturing Practice for local and foreign food, medicine and cosmetics manufacturers.

15/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 16 attached to this Regulation to get permit for branch office in Ethiopia for foreign based medicine manufacturers.

16/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 17 of attached to this Regulation to issue or renew license or for replacement of license in case of loss for of consultancy service provided in sectors which are inherently under the supervision of the Authority.

17/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 18 attached to this Regulation for inspection of Good Manufacturing Practice to be conducted abroad to register and import medicines.

18/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 19 attached to this Regulation for clinical trial control.

፲፱/ ለመድኃኒት ምዝገባ፣ ዳግም ምዝገባና ለውጥ የላቦራቶሪ ምርመራ ስራ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፳ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፳/ የባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ለሚሰጣቸው የመድኃኒት ምርመራ ስራዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፳፩ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፳፩/የባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ለሚሰጣቸው የምግብ ምርመራ ስራዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፳፪ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፳፪/የባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ለሚሰጣቸው የቶክሲኮሎጂ ምርመራ ስራዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፳፫ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

19/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 20 attached to this Regulation for registration, renewal of registration or variation of-medicine for laboratory test.

20/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 21 attached to this Regulation for the authority's service regarding laboratory test of medicines.

21/ Service fees shall be payable in accordance with the rate prescribed in a schedule 22 attached to this Regulation for the Authority's service regarding laboratory test of food.

22/ Service fees shall be payable in accordance witl the rate prescribed in a schedule 23 attached to thi Regulation for the Authority's service regardin laboratory test of toxicology.

4. <u>Effective date</u>

This Regulation shall enter in to force on the date o publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of January, 2016.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

1. **ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ አምራቾች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት፣ ለእድሳትና ምትክ የአገልግሎት ክፍያ**

**ሀ/ ተቋሙ የሚገኝበት አካባቢ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ50 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ከሆነ**

**ሰንጠረዥ 1**

| ተ. | የተቋሙ ዓይነት | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ለማግኘት በብር | ሁለተኛ ዙር የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | አዲስ የምርት መስመር መጨመር በብር | የአድራሻ ለውጥ በብር | የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ በብር | አዲስ ተቋ በተጨማሪነት ማስፈቀድ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምግብ ማምረቻ ድርጅት | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |
| 2 | የመድኃኒት ማምረቻ ድርጅት | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |
| 3 | የሕክምና መገልገያ መሳሪያ ማምረቻ ድርጅት | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |
| 4 | የኮስሞቲክስ ማምረቻ ድርጅት | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |

**Rate of Service fees to get certificate of Competency Assurance, renewal and replacement by food, medicine, medical supplies and equipment as well as cosmetics manufacturers**

**A/ If the address of the institution is at about 50km radius from the office of the Authority**

**Schedule 1**

| Types of institution | For new certificate of competence (birr) | For renewal of certificate competence (birr) | For replacement (birr) | $2^{nd}$ round pre license inspection (birr) | $3^{rd}$ round pre license inspection (birr) | Add new production line (birr) | Change of place (birr) | Change of professional or institution name (birr) | Authorization additional new facility (birr) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Food producer | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |
| Medicine producer | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |
| Medical equipment and supplies producer | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |
| Cosmetics producer | 1150.00 | 400.00 | 400.00 | 1450.00 | 1700.00 | 1150.00 | 1150.00 | 400.00 | 1150.00 |

ለ/ ተቋሙ የሚገኝበት አካባቢ ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤቱ ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ ባለ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን

ሰንጠረዥ 2

| የተቋሙ ዓይነት | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ለማግኘት በብር | ሁለተኛ ዙር የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | አዲስ የምርት መስመር መጨመር በብር | የአድራሻ ለውጥ በብር | የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ በብር | አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ማስፈቀድ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የምግብ ማምረቻ ድርጅት | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |
| የመድኃኒት ማምረቻ ድርጅት | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |
| የሕክምና መገልገያ መሳሪያ ማምረቻ ድርጅት | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |
| የኮስሞቲክስ ማምረቻ ድርጅት | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |

B/ **<u>If the address of the institution is at more than 50km distance from the office of the Authority</u>**

**Schedule 2**

| Type of institution | For new certificate of competence (Birr) | For renewal of certificate competence (Birr) | For replacement (Birr) | 2nd round pre license inspection (Birr) | 3rd round pre license inspection (Birr) | add new production line (Birr) | Change of place (Birr) | change of professional or institution name (Birr) | Authorization additional new facility (Birr) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Food producer | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |
| Medicine producer | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |
| Medical equipment and supplies producer | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |
| Cosmetics producer | 2900.00 | 400.00 | 400.00 | 3600.00 | 4350.00 | 2900.00 | 2900.00 | 400.00 | 2900.00 |

2. ለምግብ፣ የመድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ፣ ኮስሞቲክስና ትምባሆ አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት፣ ለእድሳት፣ ምትክና ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት የአገልግሎት ክፍያ፣

<u>ሰንጠረዥ 3</u>

| የተቋሙ ዓይነት | አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳትለ ማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ለማግኘት በብር | ሁለተኛ ዙር የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | አዲስ መጋዘን ለመጨመር በብር | የአድረሻ ለውጥ በብር | የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ በብር | አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ማስፈቀድ (ቅርንጫፍ) በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የምግብ አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ድርጅት | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| የመድኃኒት አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ድርጅት | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| የሕክምና መገልገያ መሳሪያ አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ድርጅት | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| የኮስሞቲክስ አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ድርጅት | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| የትምባሆ አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋይ ድርጅት | 1300.00 | 800.00 | 800.00 | 1600.00 | 2000.00 | 1300.00 | 1300.00 | 800.00 | 1300.00 |

2. **Rate of Service fees to get certificate of competency assurance, renewal, the replacement and related services by food, medicine, medical equipment and supplies, cosmetics and tobacco, importer, exporter and distributor**

**Schedule 3**

| Types of institution | For new certificate of competence (Birr) | For renewal of certificate competence (Birr) | For replacement (Birr) | 2nd round pre license inspection (Birr) | 3rd round pre license inspection (Birr) | add new store (Birr) | Change of place (Birr) | change of professional or institution name (Birr) | Authorization additional new facility (Branch) (Birr) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Food import, export and distribution | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| Medicine import, export and distribution | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| Medical equipment and supplies import, export and distribution company | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| Cosmetics import, export and distribution company | 650.00 | 400.00 | 400.00 | 800.00 | 1000.00 | 650.00 | 650.00 | 400.00 | 650.00 |
| Tobacco import, export and distribution company | 1300.00 | 800.00 | 800.00 | 1600.00 | 2000.00 | 1300.00 | 1300.00 | 800.00 | 1300.00 |

3. **Rate of Service fees to get license, for renewal and replacement for institutions requiring special license for medicine Purchase**

**Schedule 4**

| No | Service sector | Reason for payments in Birr | | |
|---|---|---|---|---|
| | | New license | Renewal | Replacement |
| 1 | Medicine Purchase license for hospital | 400.00 | 400.00 | 400.00 |
| 2 | Medicine Purchase license for health center | 400.00 | 400.00 | 400.00 |
| 3 | Medicine Purchase license for clinic | 400.00 | 400.00 | 400.00 |

4. **Rate of Service fees for Health Professionals Registration and License**

**Schedule 5**

| No | Educational level of the Professional | For new registration and license in Birr | For re-newel of registration and license in Birr | To replace registration and license in Birr |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Specialist Doctor and PhD | 100 | 50 | 50 |
| 2 | Medical Doctor | 100 | 50 | 50 |
| 3 | Second Degree | 100 | 50 | 50 |
| 4 | First Degree | 100 | 50 | 50 |
| 5 | Diploma | 100 | 50 | 50 |
| 6 | Certificate | 100 | 50 | 50 |

5. **Rate of Service fees for issuance of health professionals' registration certificate for foreigners, who will be employed in Ethiopia and an Ethiopian will going to work in a foreign country and for issuance of letter of good standing.**

**Schedule 6**

| No | Educational level of the Professional | For new registration and license in USD | For re-newel of registration and license in USD | To replace registration and license in USD |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Letter of good standing | 100.00 | 50.00 | 50.00 |
| 2 | For a form to be filled by the requesting country where the health professionals is to be employed | 100.00 | 50.00 | 50.00 |
| 3 | For registration of foreigners any level health professionals who will stay and practice more than three months in Ethiopia | 100.00 | 50.00 | 50.00 |

6. የጤና ተቋማት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት፣ ለእድሳት፣ ለምትክ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን፣ አዲስ የአገልግሎት ዘርፍ ለመጨመር፣ የአድራሻ የባለሙያና የድርጅትስም ለውጥ ለማድረግና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ የአገልግሎት ክፍያ

ሰንጠረዥ 7

| ተ.ቁ | የተቋሙ ዓይነት | አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ለማግኘት በብር | የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ለማግኘት በብር | ሁለተኛ ዙር የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በብር | አዲስ የአገልግሎት ዘርፍ ለመጨመር በብር | የአድረሻ ለውጥ በብር | የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ በብር | አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ማስፈቀድ (ቅርንጫፍ) በ- |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.00 |
| 2 | ሐኪምና ከዛ በላይ የሆኑ የጤና ባለሙያዎችን የሚያሰለጥኑ የትምህርትና የጤና ተቋማት | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.00 |
| 3 | ስፔሻላይዝድ የጤና ማዕከላት | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.00 |
| 4 | ክልል ተሻጋሪ የሕክምና ተቋማት | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.00 |

6. **Rate of Service fees for health professional new certificate of competency confirmation, renewal, replacement, 2nd and 3rd round pre license inspection; add new services. Address, name and profession change and organization to authorize new facility.**

**Schedule 7**

| No | Type of institution | For new certificate of competence (birr) | For renewal of certificate competence (birr) | For replacement (birr) | 2nd round pre license inspection (birr) | 3rd round pre license inspection (birr) | add new service (birr) | Change of place (birr) | change of professional or institution name (birr) | Authoriza n additio new facil (branch (birr) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Specialized hospitals | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.0 |
| 2 | physician and above health professionals them get trained School and health institution | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.0 |
| 3 | Specialized health facilities | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.0 |
| 4 | Cross regional health institutions | 1600.00 | 400.00 | 400.00 | 2000.00 | 2400.00 | 1600.00 | 1600.00 | 400.00 | 1600.0 |

7. **<u>ምግብ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ወይንም ወደ ውጭ ሀገር ሲላክ በመግቢያና መውጫ በር ለቁጥጥር የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፣</u>**

**<u>ሰንጠረዥ 8</u>**

| ተ.ቁ | የግብዓት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | ለአንድ ዓይነት ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ምግብ ቁጥጥር በቶን | 10 |
| 2 | ከአንድ ዓይነት በላይ ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ምግብ ቁጥጥር በቶን ብር አስር ከሚከፈለው በተጨማሪ በእያንዳንዱ ምርት ዓይነት ተጨማሪ ክፍያ | 4 |
| 3 | ወደ ውጭ አገር ለሚላክ የኤክስፖርት ምርት ቁጥጥር በቶን | 4.50 |

8. **<u>በመግቢያ መውጫ በሮች ላይ ለሚካሄድ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ ኮስሞቲክስና የኮስሞቲክስ ጥሬ ዕቃዎች ትምባሆና ለአስከሬን ቁጥጥር የአውሮፕላን እርጭት የአገልግሎት ክፍያ፣</u>**

**<u>ሰንጠረዥ 9</u>**

| ተ.ቁ | የግብዓት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች | 350.00 |
| 2 | የሕክምና መገልገያ መሳሪዎች | 350.00 |
| 3 | የኮስሜቲክስ የኮስሜቲክስ ጥሬ ዕቃዎች | 350.00 |
| 4 | ትምባሆ | 700.00 |
| 5 | የአስከሬን ቁጥጥር (ወደ ውጭ ለሚወጣ) | 150.00 |
| 6 | ለአውሮፕላን ርጭት | 350.00 |

9. **<u>በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ ለሚካሄድ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ፣ ኮስሞቲክስና የኮስሞቲክስ ጥሬ ዕቃዎችና የትምባሆ ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ፣</u>**

**<u>ሰንጠረዥ 10</u>**

| ተ.ቁ | የግብዓት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች | 150.00 |
| 2 | የሕክምና መገልገያ መሳሪዎች | 150.00 |
| 3 | የኮስሜቲክስ የኮስሜቲክስ ጥሬ ዕቃዎች | 150.00 |
| 4 | ትምባሆ | 300.00 |

7. **Rate of Service fees for inspection of import and export food in entry-exit gates**

**Schedule 8**

| No | Types of input | Fee in Birr |
|---|---|---|
| 1 | For control of one item of food which is imported in ton | 10 |
| 2 | For more than one imported item food control the services fee ten birr per ton and an additional fee for each extra item | 4 |
| 3 | For control of export products in tone | 4.50 |

8. **Rate of Service fees for import of medicine and medicine raw materials, medical supplies and equipment, cosmetics and cosmetics raw materials: tobacco and dead body control and airplane fumigation service**

**Schedule 9**

| No | Type of input | Fee in Birr |
|---|---|---|
| 1 | Medicine and medicine raw materials | 350.00 |
| 2 | Medical devices | 350.00 |
| 3 | Cosmetics and cosmetics raw materials | 350.00 |
| 4 | Tobacco | 700.00 |
| 5 | Dead body control (to be export) | 150.00 |
| 6 | Airplane fumigation | 350.00 |

9. **Rate of Service fees for export of medicines and medicine raw materials, medical supplies and equipment, cosmetics and cosmetics raw materials and tobacco control for the items to be exported**

**Schedule 10**

| No | Type of input | Fee in Birr |
|---|---|---|
| 1 | Medicines and medicine raw materials | 150.00 |
| 2 | Medical devices | 150.00 |
| 3 | Cosmetics and cosmetics raw materials | 150.00 |
| 4 | Tobacco | 300.00 |

10. በውጭ ሀገር የሚገኝ የምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ኩባንያ ወኪል ለመሆን ፈቃድ ለማግኘት የወኪል ለውጥ፣ ተጨማሪ ወኪል ለማስመዝገብ፣ ለእድሳትና ለምትክ የአገልግሎት ክፍያ፣

ሰንጠረዥ 11

| ተ.ቁ | በውጭ የሚገኝ ተቋም ወኪል ለመሆን (የዘርፍ ዓይነት) | ለመጀመሪያ ጊዜ በዩኤስዲ | የወኪል ለውጥ በዩኤስዲ | ተጨማሪ ወኪል ስለማስመዝገብ በዩኤስዲ | እድሳት ወይም ምትክ በዩኤስዲ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምግብ ምርት | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |
| 2 | የመድኃኒት ምርት | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |
| 3 | የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |
| 4 | የኮስሜቲክስ ምርት | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |

11. ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ለማስመዝገብ ለሰነድ ቅድመ ግምገማ ማጣራት፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ማጣሪያ ሰነድ ግምገማ ስራ የአገልግሎት ክፍያ፣

ሰንጠረዥ 12

| ተ.ቁ | የግብዓት ዓይነት | ለመጀመሪያ ጊዜ በብር | ለሁለተኛ ጊዜ በብር | ለሦስተኛ ጊዜ በብር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መድኃኒት | 400 | 500 | 600 |
| 2 | ምግብ | 350 | 450 | 550 |
| 3 | የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች | 350 | 450 | 550 |
| 4 | ኮስሞቲክስ | 350 | 450 | 550 |

12. ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ለማስመዝገብ ለሰነድ ግምገማ፣ ለዳግምና ለዋና እና ለአነስተኛ ልዩነት ምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ፣

ሰንጠረዥ 13

| ተ.ቁ | የግብዓት ዓይነት | ለሰነድ ግምገማ በብር | ዳግም ምዝገባ በየአራት ዓመት በብር | ለዋና ልዩነት በብር | ለአነስተኛ ልዩነት በብር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በጽንስ ስም የሚጠራ መድኃኒት | 1500 | 1000 | 1000 | 750 |
| 2 | ባዮ ኢኩዩቫለንስ የሚያስፈልገው መድኃኒት | 2100 | 1000 | 1000 | 750 |
| 3 | አዲስ መድኃኒት ለመጀመሪያ ጊዜ አገር ውስጥ ሲገባ | 2100 | 1000 | 1000 | 750 |
| 4 | ምግብ | 1300 | 870 | 870 | 650 |
| 5 | የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች | 1300 | 870 | 870 | 650 |
| 6 | ኮስሞቲክስ | 1300 | 870 | 870 | 650 |

10. **Rate of Service fees for the registration of agent, agent change, additional agent registration renewal and replacement of agency for the company of food, medicine, medical devices and equipment and cosmetics**

**Schedule 11**

| No | Agent for the institution in foreign based (type of sector) | For the first time in USD | Agency replacement in USD | Registration additional agency in USD | Renewal or replace ment in USD |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Food product | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |
| 2 | Medical product | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |
| 3 | Medical devices and equipment | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |
| 4 | Cosmetics product | 50.00 | 50.00 | 50.00 | 50.00 |

11. **Rate of Service fees for the registration, pre-screening of the dossier, 2nd and 3rd round pre-screening of the dossier against food, medicine, medical equipment and devices and cosmetics**

**Schedule 12**

| No | Type of input | For the first time in Birr | For the second time in Birr | For the third time in Birr |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Medicine | 400 | 500 | 600 |
| 2 | Food | 350 | 450 | 550 |
| 3 | Medical devices and equipment | 350 | 450 | 550 |
| 4 | Cosmetic | 350 | 450 | 550 |

12. **Rate of Service fees for registration, dossier evaluation, re-registration, major and minor variation of Food, medicine, medical devices and equipment and cosmetics**

**Schedule 13**

| No | Type of input | For dossier evaluation in Birr | Re-registration in every four years in Birr | Major variation in Birr | Minor variation in Birr |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Generic Medicine | 1500 | 1000 | 1000 | 750 |
| 2 | Generic Medicines with bioequivalence | 2100 | 1000 | 1000 | 750 |
| 3 | New medicine | 2100 | 1000 | 1000 | 750 |
| 4 | Food | 1300 | 870 | 870 | 650 |
| 5 | Medical devices and equipment | 1300 | 870 | 870 | 650 |
| 6 | Cosmetic | 1300 | 870 | 870 | 650 |

13. ለሚወገዱ ግብዓቶች በቦታው በመገኘት በአግባቡ መወገዱን ለማረጋገጥና ለሰርተፊኬት ዝግጅት የአገልግሎት ክፍያ፣

ሰንጠረዥ 14

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | አገልግሎት ላይ የማይውል ግብአት ማስወገድ | 1450.00 |

ማስታወሻ ስራው ከአንድ ቀን በላይ ከወሰደ ባለሙያዎች በቆዩበት ቀን ተሰልቶ የአበል ክፍያ ተጨማሪ የሚታሰብ ይሆናል፡፡

14. የመድኃኒት ምርት ሰርተፊኬት፣ ለሕክምና መገልገያዎች ሰርተፊኬት እንዲሁም ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር የምግብ፣ መድኃኒትና ኮስሞቲክስ አምራቾች የመልካም አመራረት ስርዓትን ተከትለው ስለማምረታቸው የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና ለእድሳት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፤

ሰንጠረዥ 15

| ተ.ቁ | የሰርተፊኬት ዓይነት | ለመጀመሪያ ጊዜ በብር | እድሳት በየ3 ዓመት በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | የመድኃኒት ምርት ሰርተፊኬት | 250.00 | 200.00 |
| 2 | ለሕክምና መገልገያዎች ሰርተፊኬት | 250.00 | 200.00 |
| 3 | የመልካም አመራረት ስርዓትን ማረጋገጫ ሰርተፊኬት | 250.00 | 200.00 |

15. በውጭ ሀገር የሚገኙ የመድኃኒት አምራች ኩባንያዎች በአገር ውስጥ ለሚከፍቱት ወኪል ቢሮዎች እውቅና ለማግኘት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፣

ሰንጠረዥ 16

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን በዩኤስዶ | |
|---|---|---|---|
| | | አዲስ | እድሳት |
| 1 | በውጭ ሀገር የሚገኝ ካምፓኒ ወኪል ቢሮ በአገር ውስጥ ለመክፈት | 100 | 50 |

13. **Rate of Service fees for monitoring proper disposal and to prepare certificate for the same.**

**Schedule 14**

| No | Types of Service | Fee in Birr |
|---|---|---|
| 1 | For monitoring proper disposal and to prepare certificate | 1450.00 |

N.B: if the work takes more than a day the allowance will be calculated as per the number of days the professional stay.

14. **Rate of Service fees for Certificate of pharmaceutical product, Medical supply free sale certificate, local and foreign food, medicine and cosmetics producers Good Manufacturing Practice and for renewal**

**Schedule 15**

| No | Type of certificate | for the first time in Birr | for the renewal in every three years in Birr |
|---|---|---|---|
| 1 | Certificate of pharmaceutical products | 250.00 | 200.00 |
| 2 | Medical supplies free sale certificate | 250.00 | 200.00 |
| 3 | Good Manufacturing Practice | 250.00 | 200.00 |

15. **Rate of Service fees for recognition of branch office in Ethiopia for a foreign based medicine manufacturers**

**Schedule 16**

| No | Types of Service | Fee in USD | |
|---|---|---|---|
| | | New | Renewal |
| 1 | To open branch office in Ethiopia for a foreign based medicine manufacturers | 100 | 50 |

<u>ባለስልጣኑ ቁጥጥር በሚያካሂድባቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለማስተናገድና ለፈቃድ እድሳትና ምትክ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፣</u>

## ሰንጠረዥ 17

| ተ.ቁ | የምክር አገልግሎት የሚሰጥበት ዘርፍ | ለመጀመሪያ ጊዜ በብር | እድሳት በብር | ምትክ በብር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ማንኛውም ባለስልጣኑ ቁጥጥር ለሚያደርግበት ዘርፍ | 200.00 | 100.00 | 100.00 |

<u>መድኃኒትን በአገር ውስጥ ለማስመዝገብና ለማስመጣት በውጭ ሀገር የሚካሄድ የመልካም አመራረት ቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ፣</u>

## ሰንጠረዥ 18

| ተ.ቁ | | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን በዩኤስዲ |
|---|---|---|---|
| 1 | | ለአንድ ማምረቻ ድርጅት በአንድ ማምረቻ ቦታ እስከ ሁለት ለሚደርሱ የምርት መስመሮች | |
| | ሀ | ለምስራቅ አፍሪካ አገሮች | 5400.00 |
| | ለ | ከምስራቅ አፍሪካ አገሮች ውጭ ሌሎች አፍሪካ አገሮች | 6930.00 |
| | ሐ | ለመካከለኛ ምስራቅ አገሮች | 7750.00 |
| | መ | ለሩቅ ምስራቅ አገሮች | 7400.00 |
| | ሠ | ለላቲን አሜሪካ አገሮች | 8950.00 |
| | ረ | በጠንካራ ተቆጣጣሪ አካላት የመልካም አመራረት ሰርተፊኬት የተሰጣቸው አምራቾች በቀጥታ ምርታቸውን አስመዝግበው ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ለሚያቀርቡት ጥያቄ የተቋማቱን መረጃ ለመገምገም | 3500.00 |
| | ሰ | አውሮፓ ውስጥ ያሉ ነገር ግን በጠንካራ ተቆጣጣሪ አካላት የመልካም አመራረት ሥርዓት ሰርተፊኬት ያልተሰጣቸው አምራቾችን ለመጎብኘት | 7750.00 |
| | ሸ | ሰሜን አሜሪካ ውስጥ ያሉ ነገር ግን በጠንካራ ተቆጣጣሪ አካላት የመልካም አመራረት ሥርዓት ሰርተፊኬት ያልተሰጣቸው አምራቾችን ለመጎብኘት | 8950.00 |
| 2 | | ከአራት በላይ ለሆነ ለእያንዳንዱ ሌላ ተጨማሪ የምርት መስመር | 1500.00 |
| 3 | | በአንድ ሳይት ላይ በአንድ ሀገር ውስጥ ምርቶቻቸው በተለያዩ ከተሞች ለሚገኙ ማምረቻ ድርጅቶች ለሚደረግ የመልካም አመራረት ቁጥጥር | |
| | ሀ | የጥሬ ዕቃና ያለቁ ምርቶች ማከማቻ መጋዘን | 3000.00 |
| | ለ | ያለቁ ምርቶች አሰተሻሸግ ጥራት ቁጥጥርና ስርጭት ፈቃድ | 2500.00 |
| | ሐ | ጥራት ቁጥጥርና ስርጭት ፈቃድ | 2000.00 |
| 4 | | ማንኛውም ከመድኃኒት ምዝገባ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የቅድሚያ ይሰጠኝ ጥያቄ | በየክፍያ ርዕሱ የተገለፀውን እጥፍ ክፍያ ይፈጽማል |

**Rate of Service fees for consultancy service, obtaining license, license renewal and replacement for service sectors under the control of the authority**

**Schedule 17**

| No | Sector for consultancy service | for the first time in Birr | for renewal in Birr | for replacement in Birr |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Sectors under the control of the authority | 200.00 | 100.00 | 100.00 |

**Rate of Service fees for inspection of Good Manufacturing Practice on Foreign based medicine manufacturers, to get medicine registration**

**Schedule 18**

| No | | Type of service | Fee in USD |
|---|---|---|---|
| 1 | | For one production institution one production place Up to two production line | |
| | A | East African countries | 5400.00 |
| | B | Other African countries except east African countries | 6930.00 |
| | C | Middle east countries | 7750.00 |
| | D | Far east countries | 7400.00 |
| | E | Latin American Countries | 8950.00 |
| | F | To conduct desk audit for the companies that have been granted with certificate of good manufacturing practice through strong regulatory authorities and are interested to import their products in to the country | 3500.00 |
| | G | To inspect manufacturers in Europe which are not given good manufacturing practice certificate by strong regulatory authorities | 7750.00 |
| | H | To inspect manufacturers in North America which are not given good manufacturing practice certificate by strong regulatory authorities. | 8950.00 |
| 2 | | If the production line have more than four, for each additional one line | 1500.00 |
| 3 | | Control for good manufacturing practice if the manufacturing companies having products in different towns within one site in a country | |
| | A | Warehouse for raw materials and finished products | 3000.00 |
| | B | For packaging of finished product, quality control and distribution license | 2500.00 |
| | C | Quality control and distribution license | 2000.00 |
| 4 | | Any priority of service in relation to medicines registration | Based on each fee double payment |

18. <u>የሕክምና ሙከራ ቁጥጥር የአልግሎት ክፍያ</u>

**<u>ሰንጠረዥ 19</u>**

| ተ.ቁ | የሕክምና ሙከራ | የክፍያ መጠን በዩኤስዲ |
|---|---|---|
| 1 | በተመዘገበ መድኃኒት ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ | 2150.00 |
| 2 | ባልተመዘገበ መድኃኒት ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ | 3000.00 |
| 3 | ሌሎች የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች፣ ተጨማሪ ምግቦች፣ እጽዋትና ሌሎች ለሕብረተሰብ ጤና አገልግሎት የሚውሉ ግብአቶች ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ | 1500.00 |
| 4 | በሕክምና ሙከራ ላይ ለሚቀርብ የለውጥ ጥያቄ ለውጡ ቴክኒካልና መሠረታዊ ከሆነ | 500.00 |
| 5 | ለሕክምና ሙከራ ቀላል እርማት ወይም ማስተካከያ ከሆነ | 100.00 |

19. <u>ለመድኃኒት ምዝገባ ፣ ዳግም ምዝገባና ለውጥ የላቦራቶሪ ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ</u>

**<u>ሰንጠረዥ 20</u>**

| ተ.ቁ | የምዝገባ መለኪያ | | የክፍያ መጠን በዩኤስዲ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከውጭ ሀገር ለሚገቡ መድኃኒቶች | | |
| | ሀ | አዲስ ምዝገባ | 924 |
| | ለ | ዳግም ምዝገባ | 924 |
| | ሐ | ለውጥ | 924 |
| 2 | የሀገር ውስጥ መድኃኒቶች | | የክፍያ መጠን በብር |
| | ሀ | አዲስ ምዝገባ | 1000 |
| | ለ | ዳግም ምዝገባ | 500 |
| | ሐ | ለውጥ | 500 |

**18. Rate of Service fees for Clinical Trial Control**

**Schedule 19**

| No | Clinical Trial | Service Fee in USD |
|---|---|---|
| 1 | Clinical trial to be conducted on registered medicines | 2150.00 |
| 2 | Clinical trial to be conducted on un registered medicines | 3000.00 |
| 3 | Clinical trial to be conducted on other medical supplies and equipment, food supplement items, vegetable and other community health services input. | 1500.00 |
| 4 | Change request on clinical trial if the change is technical and major | 500.00 |
| 5 | Minor correction or amendment for clinical trial | 100.00 |

**19. Rate of Service fees for laboratory test for medicine registration, re-registration, and variation**

**Schedule 20**

| No | | Type of registration | Fee in USD |
|---|---|---|---|
| 1 | Medicines to be imported | | |
| | A | New Registration | 924 |
| | B | Re- Registration | 924 |
| | C | Variation | 924 |
| 2 | New local pharmaceutical products | | Fee in Birr |
| | A | New Registration | 1000 |
| | B | Re-registration | 500 |
| | C | variation | 500 |

**Rate of Service fees for medicine laboratory tests**

**Schedule 21**

| No | Test parameters | Fee in USD |
|---|---|---|
| 1 | **Physical characteristics:**<br>Appearance, Description, Presentation, Color and Clarity of solution | 15.00 |
| 2 | **Uniformity of Mass:**<br>2.1. Tablets<br>2.2. Capsules | 20.00<br>25.00 |
| 3 | **Identification (color test)**<br>3.1. Two or less reagents<br>3.2. More than two reagents | 30.00<br>40.00 |
| 4 | **Identification (other than color test)**<br>UV-Vis<br>HPLS, TLC, GC, AAS, FTIR | 30.00<br>50.00 |
| 5 | **Related Substances:**<br>5.1. Chromatographic (HPLC)<br>5.2. Chromatographic (TLC) | 125.00<br>50.00 |
| 6 | **Uniformity of Content:**<br>6.1. Chromatographic (HPLC,GC)<br>6.2. Spectrophotometric (UV-Vis) | 300.00<br>250.00 |
| 7 | Limit test | 50.00 |
| 8 | Optical rotation | 50.00 |
| 9 | **Dissolution:**<br>9.1. Chromatographic (Normal)<br>9.2. Chromatographic (Slow Release)<br>9.3. Chromatographic (Comparative)<br>9.4. spectrophotometer (Normal)<br>9.5. spectrophotometer (Slow release)<br>9.6. spectrophotometer (Comparative)<br>9.7. Titrimetric (Normal) | 250.00<br>300.00<br>400.00<br>200.00<br>250.00<br>300.00<br>200.00 |
| 10 | **Assay:**<br>10.1. Titrimetric<br>10.2. Chromatographic<br>103. spectrophotometer<br>10.4. titrimetric with Extraction<br>10.5. chromatographic with extraction<br>10.6 spectrophotometer with extraction | 100.00<br>175.00<br>150.00<br>150.00<br>225.00<br>200.00 |
| 11 | **Other tests :**<br>11.1. loss on drying<br>11.2. pH<br>11.3. Friability<br>11.4. Moisture Content<br>11.5. Fill volume<br>11.6. Average weight<br>11.7. Melting point | 30.00<br>15.00<br>15.00<br>50.00<br>15.00<br>15.00<br>50.00 |
| 12 | **Microbiological analysis :**<br>12.1. Microbiological Assay<br>12.2. Sterility<br>12.3. Microbial limit test<br>12.4. Bacterial Endotoxins | 150.00<br>200.00<br>150.00<br>150.00 |
| 13 | **Condom testing :**<br>13.1. Batch size ≤ 35000<br>13.2. Batch size 35001 – 150000<br>13.3. Batch size > 150000 | 150.00<br>175.00<br>200.00 |

1. በምግብ ላቦራቶሪ ለሚሰጡ የምርመራ አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ

ሰንጠረዥ 22

| ተ.ቁ | የምርመራ መለኪያ | የዋጋ መጠን በዩኤስዲ |
|---|---|---|
| 1 | የፊዚካል ምርመራ | 5 |
| 2 | እርጥበት | 10 |
| 3 | አመድ | 15 |
| 4 | የአሲድ ይዘት | 15 |
| 5 | መሟሟት | 10 |
| 6 | ማይክሮ ባዮሎጂ | 70 |
| 7 | ፕሮቲን | 40 |
| 8 | ጠቅላላ ካርቦሃይድሬት | 15 |
| 9 | በአሲድ የማይሟሟ አመድ | 20 |
| 10 | ቫይታሚን (እያንዳንዱ) | 60 |
| 11 | ክሩድ ፋይበር | 25 |
| 12 | ፒኤች | 10 |
| 13 | ብረት (ማዕድን) እያንዳንዱ | 40 |
| 14 | አልኮሆል | 20 |
| 15 | ጠቅላላ ጠጣር | 10 |
| 16 | ስፔሲፊክ ግራቪቲ | 10 |
| 17 | ቅባት | 35 |
| 18 | ሪፍራክቲቭ ኢንዴክስ | 10 |
| 19 | የቅባትነት አሲድ ይዘት (እያንዳንዱ) | 60 |
| 20 | በውሃ የማይሟሟ አመድ | 10 |
| 21 | ሰልፌት | 20 |
| 22 | አልካሊኒቲ | 15 |
| 23 | አዮዲን | 20 |
| 24 | የማይሟሙ በካዮች | 15 |
| 25 | የሳሙና ይዘት | 20 |
| 26 | የሳሙና ባህሪ መጠን | 20 |
| 27 | የአዮዲን መጠን | 20 |
| 28 | ፍሪ ፋቲ አሲድ | 20 |
| 29 | የሳሙና ይዘት የሌለው አካል | 25 |
| 30 | የመቅለጫ (ደረጃ) ሙቀት | 10 |
| 31 | ሶዲየም ክሎራይድ (ጨው) | 26 |
| 32 | ፔሮክሳይድ ቫልዩ | 20 |
| 33 | የጸረ ተባይ ቅሪት (እያንዳንዱ) | 80 |
| 34 | አፍላቶክሲን (እያንዳንዱ) | 65 |
| 35 | አንቲባዮቲክ ቅሪት (እያንዳንዱ) | 75 |
| 36 | ሄቪ ሜታልስ (እያንዳንዱ) | 40 |

21. **Rate of Service fees for food laboratory taste**

**Schedule 22**

| No | Test parameters | Service fee in USD |
|---|---|---|
| 1 | Physical test | 5 |
| 2 | Moisture | 10 |
| 3 | Ash | 15 |
| 4 | Acidity | 15 |
| 5 | Solubility | 10 |
| 6 | Microbiology | 70 |
| 7 | Protein | 40 |
| 8 | Total carbohydrate | 15 |
| 9 | Acid insoluble ash | 20 |
| 10 | Vitamins (each) | 60 |
| 11 | Crude fiber | 25 |
| 12 | pH | 10 |
| 13 | Metals (minerals) each | 40 |
| 14 | Alcohol | 20 |
| 15 | Total solid | 10 |
| 16 | Specific gravity | 10 |
| 17 | Fat | 35 |
| 18 | Refractive index | 10 |
| 19 | Fatty acid profile (each) | 60 |
| 20 | Water insoluble ash | 10 |
| 21 | Sulphates | 20 |
| 22 | Alkalinity | 15 |
| 23 | Iodine | 20 |
| 24 | Insoluble impurities | 15 |
| 25 | Soap content | 20 |
| 26 | Saponification value | 20 |
| 27 | Iodine value | 20 |
| 28 | Free fatty acid | 20 |
| 29 | Unsaponifable matter | 25 |
| 30 | Melting point | 10 |
| 31 | Sodium chloride (NaCl) | 26 |
| 32 | Peroxide value | 20 |
| 33 | Pesticide residue (each) | 80 |
| 34 | Aflatoxine (each) | 65 |
| 35 | Antibiotic residue (each) | 75 |
| 36 | Heavy metals (each) | 40 |

22. **የቶክሲኮሎጂ የላቦራቶር ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ**

**ሰንጠረዥ 23**

| ተ.ቁ | የምርመራ መለኪያ | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | አጣዳፊ መመረዝ | 200/ናሙና |
| 2 | የቆዳ መቆጣት ምርመራ | 200/ናሙና |
| 3 | የኢንዛይም ማገት | 30/ናሙና |
| 4 | የኬሚካል መርዞች መለየት | 175/ናሙና |

## 2. <u>Rate of Service fees for Toxicology laboratory test</u>

### Schedule 23

| No | Test parameters | fee in Birr |
|---|---|---|
| 1 | Acute Toxicity | 200/sample |
| 2 | Skin irritation test | 200/sample |
| 3 | Acetylcholine esterase inhabitation test | 30/sample |
| 4 | Screening test | 175/sample |